# <u>የውጭ ሀገር ሥልጠና ግብረ- መልስ (ሪፖርት)</u>

## <u>መግቢያ</u>

በሀገራችን ባለፉት ሁለት አሰርት ዓመታት በተካሄደው መሰረተ-ሰፊ መዋቅራዊ ለውጥ የአገልግሎት አሰጣጡ በመሻሻሉ ምክንያት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በመመዝገብ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መነሻነት በሁለተኛው የአምስት ዓመት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የተጀመረው ዕድገት በሁሉም ረገድ ቀጣይነት እንዲኖረው <u>ለሰው ሀብት ልማት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡</u>

በተለይም ሲቪል ሰርቪሱን ጊዜው ከሚጠይቀው የብቃትና የቅልጥፍና ደረጃ ጋር ለማዘመን የሰራተኛውን ሁለንተናዊ አቅም ማጎልበት ተገቢ መሆኑ ታምኖበት የመንግስት ሰራተኛው እንደ ሥራው ባህርይና እንደሚጠበቅበት ኃላፊነት እየተመዘነ የአጭርና የረጅም ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኝ የሚያስችል መርሀ-ግብር ተነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው እንደየሥራ ዘርፎቹ የስራ ፀባይና በያንዳንዱ ሠራተኛ የሥራ ኃላፊነት፣እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ የሰው ሀብት የስልጠና ፍላጎት ላይ በተቃኘ ሁኔታ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ጭምር የአጭርና የረጅም ጊዜ የስልጠና ዕድል እየሰጠ ይገኛል፡፡

በመሆኑም እኔም የዚሁ መርሀ-ግብር ተጠቃሚ በመሆን ከገበያ ልማት ዳይሬክቶሬት ከገበያ ጥናት ሰራተኞች መካከል ዕድሉን አግኝቼ ለሁለት ሳምንት የአጭር ጊዜ ሥልጠና በህንድ ሀገር ተከታትዬ ተመልሻለሁ፡፡




በዚሁ የስልጠና ቆይታዬ የቀሰምኩትን ዕውቀትና ልምድ በአጭሩ በሚከተለው ሪፖርት ያቀረብኩ ሲሆን ለስራ ባልደረቦቼም ሆነ ከገበያ ጥናት ጋር ተዛምዶ ላላቸው ሌሎች የኢንስቲትዩቱ የስራ ዘርፎች ልምድ ማካፈሉ ( Cascading ) ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ ። ስለሆነም የስልጠና ሪፖርቴን በሚከተለው ሁኔታ አደራጅቼ በቅደም ተክተል አቀርባለሁ።

**ይኸውም**

1. የስልጠናው ዓላማ ( አስፈላጊነት )
2. የስልጠናው ስፍራ
3. የስልጠናው ርዕስ ( topic)
4. የስልጠናው ይዘት ( content)
5. የስልጠናው ሂደት (Training approach)
6. ከስልጠናው የሚጠበቅ ውጤት (Result & outcome)
7. የስልጠናው ወጪ ( sponsors)
8. የታዩ ችግሮች (challenges)
9. ማጠቃለያ ( conclusion)
10. ምክረ ሃሳብ (recommendation)

የስልጠናው ዓላማ (አስፈላጊነት) ኢንስቲትዩቱ ካለው አጠቃላይ የስልጠና መርሀ-ግብር አንፃር የህንድ መንግስት በሰጠው አጭር የስልጠና ዕድል መሰረት እኔም ከገበያ ልማት ዲይሬክቶሬት በቅርቡ በተሰጠኝ አዲስ የስራ-መደብ መሰረት የተመደብኩበትን የሥራ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲረዳኝ ከስልጠናው አዳዲስ ጠቃሚ ሀሳቦችን እንዳገኝና ያለኝ ግንዛቤ እንዲጨምር የሚረዳ ከመሆኑም በላይ በህንድ-አፍሪካ ፎረም ስብሰባ ( India- Africa Forum Summit plate Form) በኢትዮጵያና በህንድ መንግስታት መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት የሚያጠናክር አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ስልጠናው በአትዮጵያና በህንድ መንግስታት የትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ ስምምነት ውስጥ የሚካተት ሆኖ ( International crops Research institute for the semi- arid Tropics) ICRISAT ከተባለ ድርጅት ጋር ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በገባው የስልጠና ስምምነት ሲሆን የአፍሪካ ሀገራት የግብርና ምርቶቻቸውን በጥራት ይዚው እንዴት ወደ ዓለም ገበያ መግባት እንዳለባቸው ለባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ማድረግ ነው ፡፡









ስልጠናው የተካሄደበት ሥፍራ በደቡባዊ ህንድ ተላኛና (Telangana) በሚባል ግዛት ሀይድራባድ(አንድራፕራዴሽ) ከተማ ሲሆን (International Crops research Institute) ውስጥ ነው ፡፡ ስልጠናው የተሰጠው እ.ኤ.አ. ከኖሼምበር 13-24- ባሉት 11 ቀናት ሲሆን በአጠቃላይ የደርሶ መልስ ቆይታው 15 ቀናት የፈጀ ነው ፡፡ ስልጠናው ከኔ የስራ ድርሻ ( ኃላፊነት ) ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ያለው ሲሆን ርዕሱም ( Training Program on “Entrepreneurship and Marketing skills Development ” የሚል ሲሆን ዋነኛ የስልጠናው ትኩረት የአፍሪካ ሀገራት የግብርና ምርቶቻቸውን በተለይም የእንስሳት ሀብት (Dairy-farm) አትክልትና አበባ (Horticulture) የመሳሰሉትን በተሻለ ጥራት አምርተው በዓለም ገበያ ውስጥ በመግባት ተወዳዳሪ መሆን ስለሚችሉበት ሁኔታ የሚያሳይ ቴዎሪን ከተግባር ያቀናጀ ጠቃሚ ስልጠና ነበር ፡፡

የስልጠናው ይዘት በዋናነት በአፍሪካ ውስጥ በሚገኙ የምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች አሰራርና የገበያ ትስስር ላይ ያጠነጠነ ሲሆን ይኸውም፡-

- Communication as a strategic Marketing tool food processing industry snapshot of global and African scenario,

-food product packaging

- Entrepreneurship development

-Value chain analysis and Entrepreneurship Development Plans

- Rural entrepreneurship and Food processing Technologies for Africa

- E-Commerce and Digital Marketing

- Rural Marketing African perspective

የሚሉ ንዑሳን ርዕሶች የተካተቱበት ሲሆን በይዘቱ ሰፊ ዕውቀትና ተሞክሮ የተገኘበት ነው ፡፡ የስልጠናው አካሄድ (Training approach) በጣም አሳታፊ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ልምድና እውቀት ባላቸው ምሁራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ስልጠና ነው ፡፡ በየዕለቱ ከሚሰጠው ስልጠና መጨረሻ ሰልጣኞች የቤት ስራ ሰርተው በቀጣዩ ቀን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ገለፃ የሚያደርጉበት ርዕስ የሚሰጥ ሲሆን



**ለምሳሌ ያህል**

- What is the big idea or market opportunities that you would want to develop for the rural communities in your country?
- What does the training program bring to you to help you implement the big idea back in your country?
- What is lacking to develop more business opportunities in the SME sector especially amongst small holder farmers back in your country? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመስጠት ሠልጣኞች እንደየሀገሮቻቸው ተጨባጭ ሁኔታ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ የተደረገበት ስልጠና በመሆኑ በይዘቱ እጅግ ጠቃሚ ልምድ አግኝቼበታለሁ ፡፡ በዚሁ መሰረት ከዚህ የሁለት ሳምንት የስልጠና ቆይታዬ በክፍል ውስጥና ከመስክ ጉብኝት የቀሰምኩት ዕውቀትና ያገኘሁት ልምድ ውጤቱ (out came ) በቀጣይ በተመደብኩበት የስራ ኃላፊነት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ገበያን

በማፈላለግ፣ በማጥናትና አምራችና ሸማችን በማገናኘት ለማደርገው ጥረት ትልቅ አተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ ያለኝን የስራ ተነሳሽነት ስለሚጨምርልኝ የስልጠናው ውጤት በስራዬ ላይ የሚያሳድረው በጎ-ተጽእኖ ለኔም ሆነ ለኢንስቲትዩቱ ውጤታማነት በረጅም ጊዜ ጠቃሚነቱ (out came ) የላቀ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አያጠራጥርም ፡፡



የስልጠናው ወጪ በሁለት የሚከፈል ሲሆን ይኸውም ቅድመ ስልጠና በሀገር ውስጥ በነበረ ዝግጅት ማለትም ፓስፖርት፤ ሜዲካል ፤ የሀገር ውስጥ ትራንስፖርትና ፤ የመሳሰሉ ጥቃቅን ወጪዎች የተሸፈኑት በኢንስቲትዩቱ ሲሆን የአየር ቲኬትን ጨምሮ በስልጠና ወቅት ለምግብና ለመሳሰሉት ወጪዎች የተሸፈነው ደግሞ በህንድ መንግስት በተለይም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ( ministry of external Affairs Government of India) ነው፡፡

## የታዩ ችግሮች (Challenges)

በዚህ የስልጠና ጉዞ ከነበሩት ችግሮች መካከል አንዱ በሀገር ውስጥ የነበረ ቅድመ ዝግጅት ሲሆን ይኸውም በኤምባሲው በኩል ቀጠሮ በማብዛታቸው በምልልስ ጊዜና ወጪ ማብዛት እንዲሁም ቪዛና የአየር ትኬት በተጣበበ ሰዓት ዘግይቶ በመምጣቱ ለቅድመ ዝግጅት ጊዜ ማጣት ሲሆን ሁለተኛው ችግር ደግሞ በህንድ ሀገር የገጠመ ችግር ነው፡፡

እሱም ከአዲስ አበባ ሙምባይ ደርሶ መልስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረርኩ ሲሆን ከሙሞባይ ሀይድራባድ ከተማ ደግሞ በህንድ አየር መንገድ በተከፈለልኝ ትኬት መብረር ሲገባኝ ሆኖም በምሽት ጊዜ ከመድረሳችንም በላይ የነበረው የህዝብ ብዛት ለፍተሻ ብዙ ጊዜ

ስለወሰደ በሌላ ተርሚላን ወደ ሀይድራባድ ይወስደኝ የነበረው አውሮፕላን ስላመለጠኝ 1200 ኪ ሜትር ለ14-ሰዓት ያህል በአውቶቡስ በራሴ ወጪ ሙሉ ሌሊት ለመጓዝ ተገድጃለሁ። ይኸውም ሥልጠናው እንዳያመልጠኝ ተልዕኮዬን ለማሳካት ስል የከፈልኩት መስዋዕትነት ነው።

እንዲሁም በማሠልጠኛ ኢንስቲትዩቱ በነበረኝ ቆይታ የተከፈለኝ  አበልና ለምግብ የሚከፈለው አለመመጣጠን ነው፤ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ማንኛውም ነገር በክፍያ ሲሆን ዋጋውም እጅግ ውድ በመሆኑ ክፍያው ከምግብ ተርፎ ለኢንተርኔትም ሆነ ለንፅህና መጠበቂያ ዕቃ መግዣ የሚተርፍ አልነበረም፤ የጎላ  ባይሆንም ስልጠናውን የተሳተፉ የአፍሪካ ሀገራት ከሁለት እስከ ሰባት ሰልጣኞች ሲልኩ ኢትዮጵያን የወከልኩት እኔ ብቸኛ ሰው በመሆኔ ለውይይትም ሆነ ልምድ ለማካፈል አንድ ለናቱ ነበርኩ ። እንደሌሎች ሀገራት ከኢትዮጵያም ተጨማሪ ሰልጣኞች ሄደው ቢሆን ኖሮ ጠቀሜታው ለሠልጣኞቹም ለሀገርም ስለሚሆን በስልጠና ወቅትም  ሆነ ከተመለስን በኋላ በብዙ ሃሳቦች ላይ መረዳዳት ይኖር እንደነበር አምናለሁ ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ሪፖርት መግቢያ ላይ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት ስልጠናው ከኢንስቲትዩቱ የሰው  ሀብት ልማትና የስልጠና መመሪያ ጋር ተገናዝቦ ከህንድ መንግስት በተሰጠ የስልጠና ዕድል መሰረት እንድካፈል ለተሰጠኝ ዕድል  የላቀ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ከዚህ ስልጠና ባገኘሁት ዕውቀት ፣ ልምድና ተሞክሮ መሰረት ካለኝ የስራ ልምድ ጋር በመቀመር ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን የገበያ ጥናትና የአምራች- ሸማች ትስስርን ( value chain ) በማጠናከር የሀገራችን የግብርና ምርት ማለትም እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ፤ እንዲሁም የማር ምርትና ተዋፅኦ በዓለም-ዓቀፍ ገበያ ተፈላጊነት እንዲኖራቸው በተለያዩ ሀገራት የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶችና ኤግዚቢሽኖችን በማፈላለግ ባለድርሻ አካላት የምርት ናሙናዎችን ይዘው እንዲገኙ በማስተባበርና በመምራት እንዲሁም የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ ለመርዳትና አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ስልጠናው ይረዳኛል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ።

ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ስልጠና በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በሚገኝ ዕድል ሌሎች የስራ ኃላፊነታቸው የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች እንዲሰለጥኑ ቢደረግ መልካም ነው ።

## ምክረ-ሃሳብ (Recommendation)

- ወደ ውጭ- ሀገር የሚደረግ የስልጠና ጉዞ ሁኔታው በፈቀደ መጠን ቅድመ- ዝግጅቱ ቀደም ብሎ እንዲያልቅ ቢደረግ
- ዕድሉ ከተገኘ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሚሰጥ ስልጠና ላይ ከአንድ በላይ ሠልጠኞች እንዲሳተፉ ቢደረግ በብዙ ሁኔታ ሊረዳዱ ይችላሉ ።

  ሰልጣኞች ወደውጭ ሀገር በሚሄዱበት ጊዜ የሀገራቸው አምባሳደሮች ስለሆኑ ከመሥሪያ ቤታቸው አሰራር በተጨማሪ የሀገራቸውን አጠቃላይ ሁኔታ መግለፅ እንዲችሉ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ቢደረግ መልካም ነው ።



ከዚህ ሪፖርት ጋር የስልጠና ማኑዋሉን ሙሉውን በሶፍት- ኮፒ አያይዤ (Attached) ያቀረብኩ ሲሆን ፍላጎቱ ያላቸው ሊመለከቱት ይችላሉ፡፡




ICRISAT INTERNATIONAL CROPS RESEARCH INSTITUTE FOR THE SEMI-ARID TROPICS

CGIAR ICRISAT is a member of the CGIAR System Organization

Certificate of Participation

Award this

Abayneh Gebremaryam Mariye

Upon successful completion of the training course on
**Entrepreneurship and Marketing skills development**
supported by the Ministry of External Affairs,
Government of India under the India-Africa
Forum Summit (IAFS)-III

12-25 November 2017
at ICRISAT Headquarters, Patancheru, Hyderabad, Telangana State, India.

David J Bergvinson
Director General

*አባይነህ ገ/ማርያም፣*

*የገቢያ ጥናት ሲኒየር ኤክስፐርት*

*ህዳር 2010 ዓ.ም*

*ቢሾፍቱ*